የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 17 እና 18

1. ጌታችን ወደ ደብረታቦር ተራራ ከወጣበት ምክንያት ውስጥ የማይመደበው?
ሀ) በቁሳርያ ከነቢያት አንዱ ብለውት ስለነበር ነቢያትን ጠርቶ የነቢያት ጌታ እንደሆነ ለማስመስከር ነው
ለ) በደብረታቦር የዘመነ መሳፍንቱ ባርቅ ሲሳራን ድል ስላደረገው ምሳሌውን ለመፈጸም ነው
ሐ) ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ ታቦርና አርሞንኤም በስምህ ደስ ይላቸዋል ብሎ ስለተናገረ ትንቢቱን ለመፈጸም ነው
መ) መልሱ አልተሰጠም

2. ጌታችን ወደ ደብረ ታቦር ሲወጣ ይዟቸው ከወጣቸው ሐዋርያት ውስጥ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) ጴጥሮስ ለ) ይሁዳ ሐ) ያዕቆብ መ) ዮሐንስ

3. ጌታችንና ሐዋርያቱ ከታቦር ተራራ በወረዱበት ጊዜ እስከ ትንሳኤው ድረስ ያዩትን ለማንም እንዳይናገሩ ያዘዛቸው ለምን ነበር?
ሀ) ውዳሴ ከንቱን ስለማይሻ
ለ) መከራን ወደኋላ አድርጎ ክብርን መናገር ስለማይገባ ነው
ሐ) ምትሐት ያሳያል ብለው ሰዎች በእርሱ እንዳይሰናከሉ ነው
መ) ሁሉም

4. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረታቦር ግርማ መለኮቱን ሲገልጥ ሁለቱን ነቢያት የጠራበት ምክንያት የቱ ነው?
ሀ) ሰዎች ሙሴ ወይ ኤልያስ ነው ይሉ ስለነበር የነርሱ አምላክ እንጂ እነርሱን እንዳልሆነ ለማሳየት
ለ) የሙታን እና የሕያዋን አምላክ መሆኑን ለማሳየት ከሙታን ሙሴን ሞትን ካልቀመሱት ደግሞ ኤልያስን መርጧል
ሐ) መንግስተ ሰማያት ላገቡትም ላላገቡትም እንደሆነች ሲያጠይቅ ካገቡት ሙሴን ካላገቡት ደግሞ ኤልያስን መረጠ
መ) ሁሉም

5. ጌታ የምሥጢር ሐዋርያቱን ይዞ ወደ ተራራ መውጣቱ ላይ ተራራ የምን ምሳሌ ነው?
ሀ) የወንጌል ለ) የመንግሥተ ሰማያት ሐ) የኃጢአት መ)ሀ እና ለ

6. በታቦር ተራራ ላይ ከነበሩት ውስጥ የሌለው የቱ ነው?
ሀ) ኤልያስ ለ) ሙሴ ሐ) ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ መ) ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ

7. ጌታችን ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል አህያ የሚፈጭበት ወፍጮ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቁ ባሕር ቢሰጥም ይሻለዋል ስላለበት ምክንያት ልክ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) አንድ ክርስቲያን በጉዞው ሁሉ ለሌሎች በጎ ምሳሌ እንጂ ማሰናከያ መሆን እንደሌለበት ሲናገር ነው
ለ) የሃይማኖት መሪዎች ለምእመናን በሆ ምሳሌ መሆን አለባቸው ሲል ነው
ሐ) ወልድ ዋህድ ብለው ካመኑ ምእመናን አንዱን ያሰናከለ ሰው ራሱን ማጥፋት እንደሚገባው ሲናገር ነው
መ) ከምእመናን መካከል አንዱን ያሳተውን ሰው ጽኑ ቀኖና ሰጥተው ባሕር በተባለው የንስሐ እንባ ቢያሰጥሙት ይሻለዋል

8. ጌታችን ለቅዱስ ጴጥሮስ ወንድምህን እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት ይቅር በለው ሲል
ሀ) ይቅርታ በሰባ ጊዜ ሰባት የቁጥር ስሌት ይወሰናል ሲል ነው
ለ) የወንድማችሁን በደል ከልባችሁ ይቅር በሉ ሲል ነው
ሐ) ሰባት ቁጥር በዕብራውያን ፍጹም ስለሆነ ነው
መ) ለ እና ሐ

9. "በዚኽ መኖር ለኛ በጎ ነው" ያለው ሐዋርያ የቱ ነው?
ሀ) ጴጥሮስ ለ) ዮሐንስ ሐ) ያዕቆብ መ) ኤልያስ

10."ዐይናቸውንም አቅንተው አዩ፤ ነገር ግን ከጌታችን ከኢየሱስ በቀር ያዩት ማንም አልነበረም። " ይኽ የሆነበት ምክንያት?
ሀ) ሙሴ እና ኤልያስ በዛው ቢሆኑ ኖሮ "የምወደው፣ በእርሱም ደስ የሚለኝ ልጄ ይህ ነው " የሚለው ቃል ለማን እንደተነገረ ግራ ይጋቡ ነበር
ለ) ሙሴና ኤልያስ የታዩት በምትህት ስለነበር
ሐ) ሐዋርያት ስለፈሩ ከዚህ በኋላ ሙሴን እና ኤልያስን ማየት አልቻሉም
መ) ሁሉም

11. "ነገር ግን እላችኋለሁ፣ ኤልያስ ፈጽሞ መጥቷል " ብሎ ጌታ የተናገረለት ማን ነው?
ሀ) ነቢዩ ኤልያስ
ለ) መጥምቁ ዮሐንስ
ሐ) ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ
መ) ራሱ ጌታችን፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

12. ጌታ ለሐዋርያት ሲያስተምር "እንደዚህ ሕፃን ካልሆናችሁ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም። " ብሎ ያስተማረበት ሕፃን ማን ነበር?
ሀ) ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ
ለ) ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ
ሐ) ቅዱስ አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ
መ) ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ

13. ወንድምህ አንተን ቢበድልህ_____
ሀ) በሰው ሁሉ ፊት መጀመሪያ ገስጸው
ለ) መጀመሪያ ለብቻው አድርገህ ብቻውን ምከረው
ሐ) በሰው ተመክሮ ባይመለስ ለቤተክርስቲያን ተናገር
መ) ከ ሀ በስተቀር ሁሉም

14.ሐዋርያው ጴጥሮስ ለራሱ እና ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የከፈለውን ግብር ከየት እንደሚያገኘው ጌታችን ለጴጥሮስ ነገረው?
ሀ) ከቤተ መቅደስ ለ)መንገድ ላይ ሐ)ከሚያጠምደው ዓሳ አፍ ውስጥ መ)ለ እና ሐ

15.ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሞቱ እና ስለትንሳኤው ሲነግራቸው ምን አሉ?
ሀ) እጅጉን አዘኑ ለ)ትተውት ሸሹ ሐ) ሊዋጉ ዛቱ መ)ሁሉም

16.ጌታችንን እንደ ሕፃናት ካልሆናችሁ መንግስተ ሰማያት አትወርሱም ሲል ምን ማለቱ ነው?
ሀ) እንደ ሕፃናት ቂምን የማትይዙ መሆን አለባችሁ
ለ) እንደ ሕፃናት ጨዋታን ምታበዙ መሆን አለባችሁ
ሐ) እንደ ሕፃናት ፍፁም ፍቅርን ማሳየት አለባችሁ
መ)ሀ እና ሐ

17.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ወይም ሶስት ሆነው በስሙ ለሚሰበሰቡ ምን ቃል ገብቶላቸዋል?
ሀ) መላእክትን ልኮ እንደሚያፅናናቸው
ለ) ቸል እንደሚላቸው
ሐ) በመካከላቸው እንደሚገኝ
መ)ሁሉም

18.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ከሰጣቸው ስልጣን ውስጥ የሚመደበው የቱ ነው?
ሀ) እንዳሻቸው ወደሰማይ የማረግ ስልጣን
ለ) በምድር ያሰሩት በሰማይ የታሰረ መሆኑ
ሐ) በምድር የፈቱት በሰማይ የተፈታ መሆኑን
መ) ለ እና ሐ

19.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንድሞቻችን ይቅር ማለት እንዳለብን በምን ምሳሌ አስተማረ?
ሀ) እዳው በተተወለት ባርያ ለ) በሰናፍጭ ቅንጣት ሐ) ዘርን በሚዘራው ዘሪ መ) በእርሾ

20. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ ምዕራፍ 17 ላይ ደቀ መዛሙርቱ ጋኔኑን ማውጣት ባቃታቸው ጊዜ አስቀድሞ ማንን ነቀፈ?
ሀ)ሕዝቡን ለ)ጋኔኑን ሐ) ራሱን መ)ሁሉም

21.ደቀ መዛሙርቱ ጋኔኑን ማውጣት ያቃታቸው ለምንድን ነው?
ሀ)ስለእምነታቸው መጉደል
ለ) ይህ አይነቱ ያለጾም እና ያለጸሎት ስለማይወጣ
ሐ) ጨረቃ ስላልወጣ
መ) ሀ እና ለ